# በኢትዮጲያ ለጎሳ ፖለቲካ መሪዎች እንዲሁም ለሀገር ሽማግሊዎች እና ለሀይማኖት መሪዎች Apr 28 /2015

ወቀተሉ ፈላሴ ወይቤሉ ኢይሬኢ እግዚአብሄር ወኢየአምር አምላከ ያዕቆብ
ስደተኛውን ገደሉ እግዚአብሄር አያይም የያዕቆ አምላክ አያስተውልም አሉ መዝ 93

ዛሬ በሊቢያ በረሀ በማንነታቸው ላይ የመጣውን ጥያቄ በአግባቡ መልሰው መሀተባቸውን አጥብቀው ጨካኞች ያቀረቡላቸውን መራራ ጽዋ ተጎንጭተው ገዳዮቻቸውን በሞታቸው አሸንፈው ሞቶ ማሸነፍን አሳይተዋቸው የክብር ሞት ሞተዋል ከሊቢያ ካሉ ወገኖቻችን እንደሰማነው ሀይማኖት ቀይሮ መዳን ተጠይቀው እነሱ እንደሚሉት መስቀሉን ተከትሎ መሞት ሞት እንዳልሆነ አረጋግጠውላቸው አስተምረዋቸው ገዳዮቻቸውን እሾህና አመኬላ በሚበቅልባት ሁካታና መከራ የበዛባትን አለም አስታቅፈዋቸው ገዳዮቻቸው በሀሩርና በሰለት ቢገሉአቸውም 28 ሰማእታቶች ግን በጽናት ገለዋቸው ዘላለማዊ ወደ ሆነው እርስታቸው ሄደዋል አንደኛ ማህተብ ከርስትናቸው ሲሆን ሁለተኛው ማህተባቸው ኢትዮጲያዊነታቸው መሆኑን የነገሩን የመስቀልና የኢትዮጲያ ጠላቶች እንዲህ ብለዋል ጠላቶቻችን ኢትዮጲያውያን የመስቀል ተከታዮችን ገድለናል ብለው የሮከሩበትን ቪዲዮ ያየ ሁሉ ለኢትዮጲያውያን ትልቅ መልክት ልከውልናል አንዱ ኤትዮጲያዊነት ሲሆን አንዱ መስቀል ነው የተከሰሱብት ከመልከቱ የምንረዳው ተከሳሾቹ ሁለቱንም ክስ ተቀብለዋል የሚገርመው እንደሀገር እንኩአን ተመስርታ 24 አመትን ያስቆጠረችውን ኤርትራውያን ወንድሞቻችን በዚህ ክስ ተስማምተዋል ኤርትራውያን ነን ባለማለታቸው ነው እንጂ ISIS ኤርትራን ሳያዉቁ ወይም ላለመጥራት ብለው አንዳልሆነ ISIS የሚባለውን ወንጀለኛ ድርጅት አምናለሁ ይሄ የነብሰ ገዳይ ቡድን ይሚሰራውን ደብቆም ሆነ ዋሽቶ አያውቅም እግዚአብሄርንም ሰውንም የማይፈራ የዲያቢሎስ መልከተኛ ስለሆን ስለዚህ ይሄ መልክት የባልቻ እና የአያሱ ፡ የአወቀ ገመቹ እና፡ የዳንኤል አዲሽ፡ የብሩክ ካሴ ፡የኢሳኢያስ ተጫኔ ፡ የበቀለ ታጠቁ ፡እንድሁም የኤርትራውያኑ መልክት መሆኑን በግልጽ አስረድቶናል ሰለዚህ የነዚህን ሰማዕታት ቃል ፈቃዳችሁ ከሆነ በጎሳ የተደራጃችሁ አቶ ኢሳኢያስ እንዳሉን የመቶ አመት የቤት ስራ ካልሆነ በ 25 አመት ቢበቃን እባካቸሁ መከራችን በዝቶአልና የፐለቲካ መሪዎች የሀዘን መግላጫ በማውጣት የህዝብን ሀዘን ማሻር የሚቻል አይመስለኝም ሀዘናችንን ISIS አደባባይ አወጣብን እንጂ ይሄ ቡድን ሀገሪቱን ከተቆጣጠሩ ጥቂቶች የሚንደላቀቁበት ሚሊዮኑ እያዘነ ወደ መቃብር እየወረደ ያለበት ሺዎች በበረሀ እየተቅበዘበዙ ያለንበት ሰአት ነው ሰለዚህ እነሱም እያረዱን እናንተም የሀዘን መግለጫ እያወጣችሁ የምትጋዙበትን መንገድ ቆም ብላቸሁ አስቡ የተጉአዛችሁበትን ዘመን ዞር ብላችሁ ተመልከቱ እግዚአብሄር አምላክ ከፈቃዱ ሲወጡ እስራኤላውያንን የቀጣበት መንገድን ዛሬ ውንድሞቻችን እና እሀቶቻችን ሳምንት ባለሞላ ጊዜ የሚያቁአርጡትን የሲና በረሀ እግዚአብሄርን የሚያሳዝን ሰራ በመስራታቸው መንገዱን አርዝሞባቸው እናያለን ዙዳግም ም.8.ቁ 2 አምላክህ እግዚአብሄር ይፈትንህ ዘንድ በልብህ ያለውን ትዛዝ ትጠብቅ ዘንድ ያውቅ ዘንድ ሊያስጨንቅህ አርባ ዘመን የተጉአዝክበትን መንገድ አስብ።ህዝብ ያዘነበት እግዚአብሄርም ያዝንበታል ህዝብ አሳዝነን እስከ መቼ እንጉአዛለን ዛሬ የደረሰብን ሀዘን የመጀመሪያም የመጨረሻም አይደለም ከዚህ ድርጊት ባልተናነሰ በደል ግፍ በሀገራችን ምድር ተሰርቶአል ዛሬም እየተሰራ ነው ይህን በደልና ግፍ የሚለየው ISIS የገደለውን ሳይጨምርም ሳይቀንስም በቪዲዮ መረጃ ለአለም ያሳያል በኢትዮጲያ ውስጥ የተሰራውን ስቃይና በደል ግፈኞቹ ሰለማያምኑ ልዩነታቸውን በዚህ ብንቀበልም በበደሉና በግፉ ግን ሁለቱንም አንለይም የጠፋው የሰው ነበስ ነውና በኢትዮጲያ ሀገራችንም ከዚህ ዘር የመጣህ ነህ ተብሎ ሰው ታርዶአል እነደ ከብት የሰው ልጅ ቆዳውን ተገፉአል ምን ያልተሰራ ግፍ አለ ዛሬ በደረሰብን ሀዘን ከበደሉም ከግፉም በላይ ደግሞ ለበደለኞችና ለመከረኞች ጠያቂ መንግስት ማጣታቸን ሀዘኑን እጥፍ ድርብ ያደርግብናል ስለዚህ በጎሰኝነት የተደራጃችሁ ጎሰኞች የፖለቲካ መሪዎች ለምን ያሰብንበት መድረስ አቃተን ብላችሁ ወደሁአላ ዞር ብላችሁ የምትመለከቱበት ጊዜ ዛሬ ቢሆን የመቶ አመት መከራችንን ባላጋንን የመዳኛችንም ቀን ዛሬ ይሆናል እግዚአብሄር የሚሳነው ነገር የለምና እግዚአብሄር እርቅን ስለሚፈልግ መከራችንንም ያሳጥርልናል የመቶ አመት የቤት ሰራውን እኮ ዛሬ በተቃዋሚው ሰፍራ ያላችሁ ፓርላማ ውስጥ ቁጭ ብላችሁ ነው የቤት ስራውን ለኢትዮጲያ ህዝብ የተሰጠው ይሄ ሂሳብ ደግሞ ኢለመንተሪ ሂሳብ ነው መቀነስና መደመር ነው የእገሪቱን ክበር መቀነስ የህዝብን ወርደት

መደመር(መጨመር) ምን ያልቀነሰነው ምን ያልደመርነው ነገር አለ ሞታችንን እንኩአን ደምረው የሞት ሞት አድርገውታል የወያኔው ትልቁ ሹም እንዲህ አሉን አማሃራ እና ኦሮሞ ሁለተኛ አይገናኝም በሚገባ ስራ ሰርተናል አሉን አንዳንዱም ሲታይ ውነት ይመስላል አሩሲ ላይ ያቆሙት ሀውልት የዚህ ምሳሌ ሳይሆን ይቀራል አሩሲ ላይ ይህን ሃውልት ከማቆማቸው በፊት በየልባችን ውስጥ የዘረኝነት ሀውልት ማቆማቸው ብዙም አልታይ ሲለን በኢትዮጲያ ህዝብ ገንዘብ የሚቀመስ የሚበላ በጠፋበት ሰአት ሲሚንቶ እና ድንጋይ ቀላቅለው የልዩነታችሁን ሀውልት ተመልከቱ በለው አርሲ ላይ ዲንጋዩን አቆሙልን ዛሬም ተስፋዬ (ገ/ሰይጣን)ገብረ አብ ማለት እግዚአብሄር የሰራው ማለት ነው ተሰፋዬ እስከዛሬ ክሰራው በላይ ዛሬም እየደከመበት ያለው ስራ የሰይጣን ሰራ ነው ይሄ ካድሬ ስደተኛ መስሎ ሰደተኛው ውስጥ ግብቶ የተለከፈበትን የልክፍት ሰራውን አዳራሽ እየተከራየንለት ስራውን ይሰራል ዛሬ ነቢያ ተነስተው ልትጠፉ ነው ተብሎ ነጋሪ ነብይ የሚያስፈልገን አይመስለኝም እየጠፋን እያየነው እግዚአብሄር ነቢያትን መላክ ምን አስፈለገው ነቢያት እኮ በሀገራት ላይ የተላኩበት ዘመን ሳያውቁ ሲያጠፉ ከጥፋታቸው ለመመለስ ነበር ነቢያት የሚላክላቸው እኛ ግን ነቢያት አያስፈልገንም ሁላችንም የምንሰማማው በመጥፋት ላይ ነው ግን በጣም የሚያሳዝነው ማሳዘንም ብቻ አይደለም የሚመጣውን ስናስበው በቁማችን ሰንቶቻችንን እረፍት የሚነሳ ነው ስለዚህ ይህንን የዘር ቦንብ እንደተቀበረ ተላለቁ ብላችሁ ልትሄዱ ነው ? እሰከ ዛሬ የተጉዝነው ጉዞ እናንተን በቻ ሳይሆን ህዝብና ሀገርንም ወደ ወርደት ያወረደ ጉዞ ነው ውርደትን የምትረዱ ይመስለኛል ሀገር እያለን ሃገር አጥተን 30 አመት በስደት መኖር ተምንሰማይ የምናየው የኛ ወገኖችን እንግልትና ሰቃይ በሄዱበት እንደ ውሻ ሲጠየፉን አለም ሲጠላን ምነው ዝም አላችሁ ዛሬ ይብቃን ከወያኔ በትር የናንተ መለያየት ያማል የዚህ መከረኛ ህዝብ መከራ እና እንግልት ተሰምቶአችሁ ዛሬ የዚህ ህዝብ ጥያቄ ቁአንቁአ አይደለም የዚህ ህዝብ ጥያቄ መደርተኝነት አይደለም የዚህ ህዝብ ጥያቄ ስልጣን አይደለም እዬዬም ሲዳላ ነው በሀገሩ የመኖር ዋስትና የፍትህ ዋስትና የሰላም ዋስትና በሀገሩ ምድር ሰርቶ የመኖር ዋስትና ተነፍጎት በአለም ላይ ሞታችን የውሻ ሞት እየሆነ ያለው ሰለዚህ ከዚህ የውርደት አዙሪት እናንተም ህዝብም ሀገርም የምትወጣው ከመንደር እይታ ወታችሁ ትልቁአን ኢትዮጲያን ስታዩ ለኢትዮጲያውያን ሁሉ እንቆማለን ብላችሁ ስትነሱ ጠላትም ይሸበራል ከውርደት የምንወጣበት መከራችንም ያጥራል በኢትዮጲያ ታሪክም ትልቅ ሰፍራ ይይዛል ሉተር ማንዴላ ጋንዲ እያልን የምናወሳቸው ሰዎች የተለዩ ሰዎች ሆነው ሳይሆን ከቂም ከበቀል ወጥተው ለህዝብ ለጋራ ለሆነች ሀገር በመትጋታቸው ነው እኛም ምሳሌ የምንጠቅሳቸው በቅዱስ መጽሀፍ ላይ እንዲህ ይላል እናንተ የጋላቲያን ሰዎች እየሱስ እንደተሰቀለ ሆኖ በፊታችሁ ተስሎ እያያችሁ እየሱስን ላለመከተል አዚም ያደረገባችሁ ማነው ወደ አንድነት ወደ ኢትዮጲያዊነት እንዳትመጡ ምን አይነት አዚም ተደርጎባችሁ ይሆን ይሄ ሁሉ መከራ በህዝብ ላይ እየደረሰ በትናጥል ህዝብን እየገደሉ ሲፈልጋቸው እያገዳደሉን አይታችሁአል ዛሬ እርጅና እየተጫናችሁ ዘመን እያለፈባችሁ መሆኑን ተረድታችሁ የጎሳ ድርጅታችሁን አፈረአርሳችሁ በኢትዮጲያ ጥላ ሰር ተሰባስባችሁ ከችግር ሀገሪቱም ህዝቡም የሚወጣበትን መንገድ እንድትመክሩ በርግጥ እስካሁኑም ሳትጸጸቱ አትቀሩም ተከታዮቻችንስ ምን ይሉናል ትሉ ይሆናል የሰው ልጅ እድገት የአለም እድገት የምናየው በጋራ በተሰራ ሰራ ነው አለም ወደ አንድ እየመጣ እኛ ያወም ኢትዮጲያውያን ወደሁአላ መጉአዛችን ሁላችንንም እንደዜጋ ያመናል ሀገር ህዝብ ከዳነ በሁአላ ሁሉንም በመመካከር ማድረግ ይቻላል ዛሬ አለም ተቀይሮአል ዲሞክራሲያዊ ሀገር መስርቶ የሰው ልጅ ሁሉ እኩል የሚኖርባት ሀገር ማድረግ የሚቻለው በመሰማማት ነው ስለዚህ 40 አመት የተጉአዝንበትን ድርጅት እንዴት እናፈርሳለንም የሚል ደንቃራ ሀሳብ ይመጣ ይሆናል እግዚአብሄር ከሰራው ሰው የናንተ ድርጅት አይበልጥም የሰው አካል በጨካኞች እየፈረሰ ነው ትግሉ ለስልጣን ካልሆነ ሰው እናድን ከሆነ የሀይማኖት አባቶችን ይዛችሁ የሀገር ሽማግሌ ይዛችሁ ከህዝብ ጋር የምትመክሩበት ጊዜው ይሄ ጊዜ ነው በህይወት የተረፈ ህዝብ እንድታድኑ በኢትዮጲያዊነትና በመስቀል ተከታይነታቸው የተሰዉ በደማቸው ያሳዩንን በስም አወጣት ከሆነ ኦሮሞ/አማራ/ትግሬ/ጉራጌ/ኤርትራውያን ሞታቸውን በኢትዮጲያዊነት በደማቸው አትመው የሄዱት የአወቀ ገመቹ/ የባልቻ/የእያሱ / የዳኔል አዲሽ/ በቀለ/ የኢሳኢያስ / የወንድሞቻችንን ድምጽ እንድትሰሙ እያሳሰብኩ የተሳሳተ ትውልድንም ወደአንድ የማምጣት ስራ ሰርታችሁ ሀገራችንን ኢትዮጲያን እና ያአን ትልቅ ህዝብ ወደክብሩ እንድትመልሱ እና እናንተም በርጅና እድሜአችሁ

በህዝብ ከበሬታን አግኝታችሁ ቀሪ እድሜአችሁን በሰላም እንድትኖሩ እግዚአብሄር አምላክ ይረዳችሁ ዘንድ የዘወትር የህዝብ ጸሎት ነው።

## ለሀገር ሽማግሌዎችና ለሀይማኖት መሪዎች

መጽሀፈ/ምሳሌ/ም 16/31 የሸበተ ጸጉር የክብር ዘውድ ነው እርሱም በጽድቅ መንገድ ይገኛል ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጲያም ህዝቡም ተው የሚል ሽማግሌ የጠፋበት ሰአት ይመስላል የሚገጽስ መንፈሳዊ አባትም እንዲሁ ቤትኛውም እምነት አልታይ ብሎአል የራሱን እምነት ከማስፋፋትና እምነቱን ከማስከበር ውጭ የእግዚአብሄር ፍጥረት ትውልድ ወደሞት ሲነጉድ ተው ምንድን ነው ነገሩ በሎ ከመመካከር ይልቅ ሰው ከሞተ በሁአል ሰላማዊ ሰልፍ ከዛም በዘለለ መግለጫ ከማውጣት ውጭ የትውልዱን ችግር ለመቅረፍ አለያም የችግሩን መንስኤ ለመረዳት መመካከር የታየበት ጊዜ በመጥፋቱ ሀገራችንን የያዘውን ቡድን እየከሰስን እየተቃወምን 25 አመት መጣን በርግጥ እኛ ችግሩን እንዴት እንቀርፋለን ትሉ ይሆናል መጽሀፈ ምሳሌ 17/ጥቂት ቃልን የሚናገር አዋቂ ነው መንፈሱም ቀዝቃዛ የሆነ አስተውይ ነው። በርግጠኝነት ኢትዮጲያ በዚህ ደሀ አይደለችም በርካታ መንፈሳችሁ የተረጋጋ ጨዋ አዋቂ ለኢትዮጲያ አይደለም ለአለም ምክር ለትሰጡ የምትችሉ ጠቡብቶች በስደት ላይ ድምጻችሁን አጥፍታችሁ በየጸሎት ቦታዎች አንገታችሁን አቀርቅራችሁ የቅድስት ሀገራችሁ ኢትዮጲያ ወደቀት አያዘናችሁ ላላችሁ ኢትዮጲያውያን አባት እናቶቻችን በስደት በምትኖሩበት የሀገራችሁ ወርደት አሸማቁአችሁ በህዝቡ መከራ አዝናችሁ እንዳለ እናውቃለን ዛሬ እናንተም የምትጽናኑበት ሀገርም የምታድኑበት ጊዜውን እግዚአብሄር በነዚህ ሰማእታት ወንድሞች ኦሮሞ/አማራ/ትግሬ/ጉራጌ/እንዲሁምከምስራቅ ከምእራብ ከደቡብ ከሰሜን ተቀጣጥረው እንደወጡ ጠላቶቻችን ኢትዮጲያውያን የመስቀል ተከታዮችን ገደልን ብለው ፎክረውብናል ይሄ ከሞያሌ እስከ ትግራይ ከወለጋ እስከ ኦጋዴን ከግንደር እስከ አፋር ያለውን ኢትዮጲያዊ ሁሉ ከብር የሚነካ ነው ሰለዚህ ተናግራችሁ የምተሰሙ ታይታችሁ የምተከበሩ በስደት ያላችሁ እግዚአብሄር ትልቅ ያደረጋችህ የሀገር ሽማግሌዎች በሀገራችን ባህል መሰረት የሀይማኖት አባቶችን ይዛችሁ በጎሳ የተደራጁ ድርጅቶችን አስገድዳችሁ ወደ አንድነት የማምጣት ስራ ልትሰሩ ምን አልባት እግዚአብሄር ይህን እድሜ ሰጥቶአችሁ ይህን ህዝብና ይችን መከረኛ ሀገር ልታድኑ ይሆናል ይህን መከራ ያሳያችሁ ለበጎ ነው እና ከዚህ የሚበልጥ የጽድቅ ስራ ዛሬ የለም ነገን ማየት የማይችሉ 90 ሚሊየን ህዝብ ይዘው በዳሰሳ የሚቀልዱብን መሪ ተብየዎች እድሜ ማብቃት የሚቻለው በሀገሪቱ ምድር አንድነት ሲታወጅ ነው ከባድ ሊመስላችሁ ይችላል ግን ይቻላል አምላክን የያዘ ሰው አይሸነፍምና ግድ በሽምግልና የሚሰራ ሰራ ኢትዮጲያ ያስፈልጋታል በአስተዋይ ሽማግሌዎች ስትመራ የኖረች ሀገር ናትና እባካችሁ ሳታመነቱ በምትቀራረቡ ሰዎች ጀምሩና ከምስራቅ ከሰሜን ከምራብ ከደቡብ ተጠራርታችሁ ለኢትዮጲያውያን ቀን አብሩልን። **የሀይማኖት አባቶችም** በየእምነታችሁ ተመካክራችሁ እስላም ክርስቲያኑ ኦሮሞ አማህራ ትግሪ ጉራጌ ሳይሉ ከመስቀሉም ባሻገር ኢትይጲያዊነት ሀይማኖት መሆኑን በጽናት ሳይለያዩ ያተሙት የደም እዳ መሆኑን ተገንዘባችሁ በስደት የምትገኙ ሁሉ ከጽሎት በተጨማሪ ከልጆቻችሁ ጋር 40 ዘመን የመጣንበትን የዘር ፖለቲካ ሀገራችንን አዝቅት ውስጥ የከተተ መሆኑን እና ህዝቡንም ወርደት ውስጥ የከተተ መሆኑን አስገንዘባችሁ ህዝቡን ለማገናኘት ሰራ እንድትጀምሩ የደሙ ደውል ጥሪ የሊቢያ ወንድሞቻችንን በልቶ የሚቆም ሳይሆን ሀገራችንን የሃዘን ሃገር እንደማያደርግብን ዋስትና የሌለን ሀዝቦች ነን እግዚአብሄር በኪነ ጥበቡ እየጠበቃት ያለች ሀገር ብትኖር ኢትዮጲያ ነች አጼ ንብለ ድንግል እየገረፉ ጦር አምጣ እያሉ ለመኑ የሚባሉት ንጉስን ጦር አምጥቶ ሀይማኖትም ታሪከም ወድሞአል ዛሬ ሀገራችንን የያዘው ቡድንም አሸባሪነትን እየናፈቀ ብቻ ሳይሆን በረዳቶቹ በኩል ይህን ስራ እንዲሰሩበኢይዮጲያ ካላንደር 1984 ዓም 6 ኢትዮጵያውያን ክርስቲያን እና ሙስሊሞች ከአሚሪካ ሀገር ገብተው በሌላው ሀገራት የተሰራውን ሰራ በኢትዮጲያም ሙስሊሙን ለሁለት ከፍለው ቦንብ ሊያወራውሩ የተጀመረ ሴራ ሰላም ወዳድ ሙስሊሞችና አምላክ ነገሮችን አብርዶልናል የጎሳ ፖለቲካውም ቢሆን ከፍተኛ ድጋፍ የሚደረገው ኢትዮጲያን ለማፍረስ ቀድሞ ጀምሮ ሲሰራበት የነበረ ጥናት እንደሚያመላከተው የአባቶቻችንን አልበገርነት እና አንደነት የትልቅነት ሰሜት ከምን የመነጨ ነው በማለት በጥናት የተሰራብን ስራ ነው ጉልበታቸው ምንድን ነው ተብሎ ተጠንቶ ጉልበታችን ተይዞአል ዛሬ ጉልበታችን እስላም ከርስቲያን ሳይሉ ተፋቅረው የኖሩባት ምድር ጎሳና

መንደር ሳያውቁ ተጋብተው ተዋልደው የኖሩባትን ሀገር እና የህን ኩሩ ታላቅ ህዝብ አንገት ለማስደፋት ተላላኪ ሆነው የመጡብን ጥቂት የጠላት መልከተኞች ስር ወድቀን በመከራ መማቀቂያው ጊዜው ማብቂያው ሰአት ላይ ሰለሆንን መድረክ ተመቻችቶ እንድታውያዩልን እና ወደ አንድነት እንድታመጡልን ተነሳሽነት አሳዩን ለዚህም እግዚአብሄር አምላክ ይረዳችሁ ዘንድ የዘወትር የህዝብ ናፍቆት ነው ለምእመን እና ምእመናት እንዲሁም ለኢትዮጲያውያን ሁሉ ፈልገን ሳይሆን በጎሳውም በእምነቱም አቦአድነው የለያዩንን ተረድተን የወገኖቻችንን እልቂትና መከራ ማብቂያ አንድነት ነውና በደማቸው ኢትዮጲያዊነትን አትመው ኢትዮጲያዊነትን የማይነጣጠል እምነት መሆኑን ከገዳዮቻቸው አልፎ ለአለም ህዝብ ያስተጋባው ያ ደም እንዳይወቅሰን በዘር በሽታም የታወርን አይናችንን ለመግለጽ መሞከር የተቀረነውም አንድነትን ከመዘመር ውጭ መድረክ በያካባቢያችን አዘጋጅተን በእግዚአብሄርም በሰውም የሚከበሩ እናቶች አባቶች በርካታ በስደት የሚገኙ ባልተለመደና እንሱ በማያውቁት መንገድ ምክረም ባለመጠየቃቸው በእኛ ስራ አፍረው ዳር ላይ ያሉትን አቅሙ ያላቸውን ኢትዮጲያውያን ድንበር ከፍለህግር ሳናይ የጉሳ ፖለቲካ ድርጅትን ወደ አንድነት እንዲያመጡን የጎሳ ድርጅት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ መቃብር የሚገባበትን መንገድ ማመቻቸት በደጋፊው ላይ ሰለሆነ ሀላፊነቱ የተናጥል ትግልን አስቁመን ወደ አንድ የማይመጡትን አስገድደን ማምጣት የደጋፊው ሀላፊነት ነው እየፈርሰ ያለው የሰው ልጅ ነው ሮሜም 3/ የእግዚአብሄር ቤተመቅደስ እንደሆናችሁ አታውቁምን ማንም የእግዚአብሄር ቤተመቅደስን ቢያፈርስ እርሱ ይፈርሳል ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ከፖለቲካ ፓርቲ በላይ ነው ለሰው ልጅ ቅድሚያ ይሰጥ የሰውን ልጅ ከሚጎዳ ስራ መታቀብ አለብን ኢትዮጲያውያን የጎዳን እና ጠላቶቻችንን እድሜ የሰጠው የጎሳ አደረጃጀታችን አንበሳውን ሰፍራ ቢወስድም ሊሎቹም በየድርሻቸው እኔ ያልኩት ካልሆነ የኔ ፖለቲካ ድረጅት ካልቀደመ የሚል የአደጋውን ጥልቀት ያላገናዘበ ትግል ወንድሜ የመባባል ትግል በመጥፋቱ አደጋው መጠኑ ሰፍቶ ውርደታችን እለት እየጨመረ አጥፊውም እድሜ እያገኘ ከስብሰባ ሳይወጣ እዚህ ላይ ደርሰናል ስለዚህ ይህን የተበታተን መሰባሰቢያችን ጊዚ ሰለሆነ የመዳን ቀን ዛሬ ይላል የቅዱስ መጽሀአፍ ቃል የኢትዮጲያ ኦ ተ ቤ ልጆች ከነ አባ እንቶኔ ደጋፊነት ወጥተን አባቶቻችን ሞተው ያቆዮልንን ሃገርና እምነት ከነ አባ እንቶኔ በላይ ስለሆነ ሀገር ከሌለ ተዋህዶ የለችም ኢትዮጲያን ካላዳንን ሰውንም እምነትንም ማዳን አይቻልም እሰከ ዛሬ ከደረሰብን በላይ አደጋ ከፊታችን ተደቅኖአል ሰለዚህ አንድ ላይ ቆመን አስገድደን በፓለቲካውም ሆነ በእምነቱ ወደ አንድ የማምጣት ስራ ዛሬ መሰራት አለበት ያሬዳዊ ዜማ እየሰማን የኖርንበት 2 አስርት አመታት አብቅቶ መስዋታችንም ልመነችንም ወደ አምላካችን ደርሶ ቅድስት ሀገር ኢትዮጲያ የምትድንበት መንገድ ጉልበታችን ሀይላችን አንድነት ነው እያዘንን እያለቀሰን የምንቀጥልበት ጊዜ ማብቃት አለበት ይህን ሳናደርግ ብንቀር እስከወዲያኛው ከአምላክ እርቀን በሀዘን ተቆራምደን የምንኖርበትን ኑሮ መቀጠል ነው እሰከ ዛሬም በሱ ቸርንርት ከታሰበልን ሴራ ሁሉ ከልሎናል ከሁን በሁላ ዘረኝነትን መከፋፈልን በጋራ ቆመን ማውገዝ ከርስቲያናዊ ብቻ ሳይሆን ሰው በመሆን በቻ ሊሰራ የሚገባው ስራ ነው ለዚህም በጎ እና የተቀደሰ ስራ እንድንዘጋጅ እግዚአብሄር አምላክ ይርዳን ።

የነዛ የደጋግ አባቶቻችን አምላክ ቅድስት ሀገር ኢትዮጲያን ከሚፎክሩባት ጠላቶቹዋ ይከልልን በአደጋ ላይ ያለውን ህዝባችንንም ካደጋ ይሰውርልን ዘንድ አምላካችንን እንማጸነዋለን

ወንድወሰን ሰብሰቤ ሀገረ እንግሊዝ wendeyee@yahoo.co.uk